# መፍትሔው የዐማራ ተራድኦና የዕርቅ ድርጅት አይደለም

ፕሮፌሰር ጌታቸው ኃይሌ "በኢትዮጵያ ሰላምን የሚያመጣ የአማራ የተራድኦና የዕርቅ ድርጅት ያስፈልጋል "(http://www. ethiopatriots.com/pdf/YeAmara_Trado_Dirijit150315.pdf ) በተሰኘ ርዕስ የጻፉትን በመመልከት ቀጥሎ የሚቀርበው ማን ከማን ጋራ ይታረቃል? ስለምንስ ዐማራው ሕዝብ ብቻ በኢትዮጵያ ውስጥ ላሉትና ለነበሩት ፖለቲካዊና ማኅበራዊ ክንውኖች ተከሳሽ ሆኖ ይቀርባል? በግልጽ የሚታወቁ ሁለት በፍጹም የማይታረቁ ዐቢይ ነገሮች አሉ።

እነዚህም ኢትዮጵያዊነት ማለትም ኢትዮጵያዊ ብሔረተኝነትና ኅሠኝነት ናቸው። ዐማራውን ሕዝብ ለይተው በዋና ጠላትነት የፈረጁት እራሱን በኢትዮጵያዊነት እንጂ በኅሠኘት ያልታገለና የሚይታገል ብሔር/ብሔረስብ ያልሆነ ስለሆነ ነው። ዐማራው ኅብረተሰብ የኢትዮጵያ ነገዶች የአያሌ ዘመናት አብሮ መኖር የፈጠረው ማኅበረሰባዊ መስተጋብር ውጤት ነው። ፕሮፌሰር ዓለሜ እሸቴ (ሰላም ሳዕሌሁ) እንደገለጹት << ኢትዮጵያዊ የዐማራ ሕዝብ ከብዙ ነገዶች የተውጣጣ፣ ከዘመን ዘመናት እየተስፉፉ የመጣ የነገዶች ሕብረት ነው ስለምንል፣ ዐምሐራ በጊዜም ሆነ በቦታ የማይከለል ከአምስት ሽህ ዓመታት በላይ ዕድሜ ያለው፣ በሰሜን ምሥራቅ አፍሪቃ አባይ ሸለቆና አምባዎች የኖረና የሚኖር የኢትዮጵያ ሥልጣኔና ታሪካዊ ሂደት ውጤት የሆነው የተለየ "ክልል" የሌለው፣ አገሩ መላው የኢትዮጵያ ንጉሠ ነገሥት መንግሥት ግዛት የሆነ መለያ ባሕሉና ሥነ ልቦናዊ ባሕሪው ኢትዮጵያዊነት ሆኖ፣ ኢትዮጵያዊነትን ከትውልድ ትውልድ የሚያስተላልፍ ድልድይ ሕዝብ ነው። የኢትዮጵያ ሕዝብና መንግሥት የረጅም ዘመናት ታሪክ የሚያረጋግጠው በንግድ፣ በግብርና፣ በውትድርና በቤተ ሃይማኖት ለመኖር ሲባል ከሰሜን ወደ ደቡብ፣ ከደቡብ ወደ ሰሜን እንዲሁም ከምሥራቁ ወደ ምዕራብ፣ ከምዕራቡ ወደ ምሥራቅ ክፍለ ሀገራት መሰደድና በዚያም መኖር የተለመደ ሲሆን ለሃብትና ለሥልጣን ሽሚያ በገብር አልገብርም ጦርነቶች ሳቢያ የኢትዮጵያ ነገዶች በማያቋርጥ ሁኔታ ሲደባለቁና ሲከፋፈሉ፣ እንደገናም ሲዋሃዱ፤ በቋንቋ፣ በሃይማኖት፣ በባሕል ሲዳቀሉ የኖሩ በመሆናቸው ዛሬ ጥቂት ቅጥረኛ የኅሣ ልሂቃን የታሪክንና የሕብረተሰብን እድገት ሂዳት ወደኋላ ቀልብሰው በጅምላ "ኅሣ" ብሎ ደንበር ከልሎ የኢትዮጵያን ሕዝብ ልክ እንደ ፉሽስት ጣሊያን ወራሪዎች መሸንሸን የፀረ-ኢትዮጵያ ኃይሎች ሴራ ነው። >> በኢትዮጵያ ውስጥ ኅሣዎች አንዳቸውም በራሳቸው ድንበርና የኅሣ ክልል ተወስነው የኖሩበትና የሚኖሩበት "ክልል" አልነበራቸውም። በቀይ ባሕር ዳርቻና በአባይ ወንዝ ሰሜን ምሥራቅ አፍሪቃ ቁልፍ ስፍራ የኢትዮጵያ ነፃ መንግሥት ለብዙ ሽህ ዘመናት መኖሩን የማይፈልጉት ታሪካዊ ጠላቶቻችንና አገር በቀል ቅጥረኛ የኅሣ ሊሂቃንና የኅጥ አምባ ገነኖች በግልጽ ወረራና ሳያመች ደግሞ ስውር ደባቸውን እንደ ጊዜው ተስማሚ ሁኔታ በሶሻሊዝምና ኮሚኒዝም ካባ፣ ከቀዝቃዛው ጦርነት ማክተም ወዲህ ደግሞ በይስሙላ ዲሞክራሲ፣ በሃይማኖትና በጎሳ እኩልነት ሽፉን የኢትዮጵያን ሕዝቡን ከፉፍለው በማቃረን ጥንታዊት ኢትዮጵያን ከዓለም ካርታ ላይ ለማስጠፉት ታስቦና ታቅዶ የባንቱስታን አፓርታይድ የኅሣ ፖለቲካን ተግባራዊ አስድርገዋል።

በኢትዮጵያ ላይ የውጭው ኃይሎች ትኩረት ካደረጉ ብዙ ዓመታት ያለፉ ቢሆንም እንኳ በይበልጥ ስልታዊ ዕቅዳቸውን በተጠናከረ ሁኔታ ማራመድ የጀመሩት በታላቁ የኢትዮጵያ ንጉሠ ነገሥት ዳግማዊ አጤ ምኒልክ መሪነት የኢትዮጵያ ሕዝብ በአድዋ የጦር ሜዳ ላይ ድል ከተቀዳጀ በኋላ ነው። በአፍሪቃ አህጉር ቅርምትና ነጭ ያልሆኑ ሕዝብ ዘርያዎች በምዕራብ አውሮፓና ሰሜን አሜሪካ በቤተ እንስሳት /Zoological garden/ ውስጥ ከአራዊት ጋራ ለትዕይነት ይቀርቡ በነበረበት ወቅት ነው ሥልጡን ነንባይ በዘመናዊ የጦር ኃይል የተገነባ ወራሪ ሠራዊታቸውን የ"ጨለማ አህጉር" በሚሉት በአፍሪቃ ምድር ማንም የሚቋቋመው ኃይል የለም ተብሎ በሚለፈፍበት በዚያን ዘመን የኢትዮጵያ ሕዝብ ያስመዘገበው የጦር ሜዳ ጀብዱ በቅኝግዛት ቀንበር ሥር ለነበሩት የዓለም ሕዝቦች ይልቁንም ለጥቁር ዘርያዎች ሁሉ መሪ ኮከብ ሆኗል።

ከድሉ ማግሥት ጀምሮ ዐማርኛ ተናጋሪውን ወገን ለይተው ለበቀል ርምጃ ስፍራና ጊዜ ጠብቀው፣ ለዳግም ወረራ ቅድመ ዝግጅት ሲያደርጉ፤ ፀረ-ምኒልክ፡፡ ፀረ-ዐማራ፣ ፀረ-ሸዋ ባጠቃላይ ፀረ ኢትዮጵያ ፕሮፓጋንዳ ዘመቻ በሰፊው መንዛታቸው ይታወቃል።

ፈረንጅ ተብዬው የጣሊያን መጢቃ ሕዝብ በድኅነትና ሥራ አጥነት፣ በፊውዳላዊ የመሬት ይዞታና ሥርዓተ አልበኝነት፤ በጣም ዝቅተኛ የእንዱስትሪ እድገት በነበረበት ፍጹም ምስቅልቅል ሁኔታ ዱቼ ሞሶሊኒና ጀሌዎቹ ከአንደኛው የዓለም ጦርነት በኋላ ፉሽስታዊ ፓርቲ መሥርተው የመንግሥት ሥልጣን ሲይዙ፤ በሌሎቹ ማለትም በአሜሪካ፣ በእንግሊዝ፤ በፈረንሳይና በናዚ ጀርመን ቀጥታና ተዘዋዋሪ የመዋዕለ ንዋይና የፖለቲካ ድጋፍን አግኝቶ ኢጣሊያ በአድዋ ላይ የደረሰባትን በጣም አሳፉሪ ሽንፈት ለመበቀል ከ40 ዓመታት በኋላ ከሰሜን ኢትዮጵያ በተወሰደው ምድረ ባሕር (ኤርትራ) እና በደቡብ ምሥራቅ ከዛንዚባር

ገዥ ሱልጣን ሰይድ ሰይድ በገዙትና የኢጣልያ ሱማሌ ምድር ብለው ከሰየሙት መስፈሪያቸው ነዋሪውን በከፍተኛ ቁጥር በመመልመልና በአስካሪነት በማሰለፍ በዓለም በተከለከለ የመርዝ ጢስና በዘመናዊ ከባድ መሣሪያ በመታገዝ ኢትዩጵያን ከሁለት አቅጣጭያ ከሰሜንና ደቡብ ምሥራቅ በመውረር፣ በጣሊያን አገር ቁጥሩ የበረከተውን ሥራ አጥ ሕዝቧን በሰፊውና ለሙ ድንግል የኢትዩጵያ መሬት ላይ በማስፈር ጥሬ ሃብት ለመበዝበዝ ሲታቀድ፤ የፋሽስት ጣሊያን የቅኝገዥነት ወረራ በኢትዩጵያ ዘላቂ መሆን የሚቻለው ሦስት ነገሮች ከኢትዩጵያ ምድር ሲጠፉ ብቻ ነው ተብሎ ታስቧል።

እነዚህም ፩ኛ ዘውድ ፪ኛ የኦርቶዶክስ ተዋህዶ ሃይማኖት ፫ኛ የዐማራ ሕዝብ ናቸው። ያማራን ሕዝብ በሚመለከት ከፋሽስት ጣሊያን ወረራ በፊትና በአምስቱ ዓመታ የተፈጸመውን ማገናዘብ እጅግ በጣም አስፈላጊ ነው።

በወረራው ዋዜማ የኦስትሪያ ወይም ነምሳ ጀርመናዊው ሮማን ፍራየኸር ፕሮቻዝካ የተባለው ፀረ ጥቁር ናዚ <u>አበሻ ጥቁሩ አደጋ</u> (Abessinien: Die Schwarze Gefahr, Wien 1935 ) በተሰኛ ርዕስ የጻፈው፣

> <<የኢትዩጵያ ንጉሠ ነገሥት መንግሥት ከጃፓን ጋራ ተባብሮ በነጭ ዘር ላይ ያሳድማል፣ ያፍሪቃ ቅኝገዥዎች እንዲያውም መላው የነጭ ዘር መንግሥታትን ሁሉ ተጠቅተዋል። ..... በኢትዩጵያ ንጉሠ ነገሥት ግዛት ውስጥ የሚኖሩት ሕዝቦችና ልዩ ልዩ ነገዶች በጥቂት ገዥ አበሻዎች በዘር፣ በቋንቋ፣ በባሕልና በሃይማኖት የተለያዩት የራስን እድል በራስ የመወሰን መብት ቢሰጣቸው ኖሮ ያበሻን በኃይል መግዛት ይጥሉት ነበር። በግዳጅ ከአውሮፓ የባሕልና ቅኝ መገዛት የሚያመጣውን እድገትና መሻሻል እንዲያገኙ ተደርገዋል። (ገጽ 11) ....በርግጥ አንድ ዓይነት አበሻ ሕዝብ የለም፣ ያለው አነስተኛው 20% የሚደርስ ዐማራ ነው ሌሎችን የሚገዛው። ክርስቲያን ያልሆኑት ነገዶች ነፃ ሊወጡ ይፈልጋሉ፣ በግልጽ ቢጠየቁ የአውሮፓውያንን የበላይ ጠባቂነትና የተረጋገጠ እድገትና ልማት ይፈልጋሉ። (ገጽ 80-81() >>

የብሔር/ብሔረሰብ የራስን እድል በራስ መወሰን እስከ መገንጠል ሥር መሠረቱ ከፍ ብሎ የሰፈረው ሲሆን የኢትዩጵያን ሕዝብ በጎሣና በሃይማኖት ከፋፍሎ የኢትዩጵያዊነት ስሜትና ኩራትን አስጥፍቶ ለአውሮፓ ነጭ ቅኝገዥዎች ታማኝ የገሣ አባቆሮዎችን ለማዘጋጀት ነበር እንጂ ለነፃነትና ለእኩልነት አልነበረም። ነገር ግን የራስን እድል በራስ መወሰን መብት በተባበሩት መንግሥታት የተደነገገው በቅኝ ተገዥነት ቀንበር ሥር ለነበሩት የአፍሪቃ፣ የደቡብና ማዕከላዊ አሜሪካ እንዲሁም እሲያ አገሮች አርነት መውጣትን ለመደገፍ እንጅ ጥንታዊ አገሮችን እንደ ኢትዩጵያ ያሉትን በጎሣ መለያ ሸንሽኖ አሸንጓሊት መንግሥታት ለመፍጠር አይደለም። ፋሽስት ጣሊያን በ1928 ዓ.ም ኢትዩጵያን ከ300 ሺህ በላይ በሆነው ዘመናዊ የጦር ኃይል ስትወር ከ20 ሺህ በላይ የሱማሌና ከ60 ሺህ በላይ የሃማሴን ትግሬ አስካሪ ባንዳዎችን ከኤርትራ አሰልፈው በመርዝ ጢስና በዘመናዊ ጦር መሳሪያ በተለይም የጦር አውሮፕላን የኢትዩጵያን ሕዝብ

በአጠቃላይ፣ በተለይም ባማራው ሕዝበ ክርስቲያን ላይ እስከ 1933 ዓ.ም ድረስ የተፈጸመው ጭፍጨፋና እልቂት እጅግ በጣም ከፍተኛ እንደነበር በሰፊው ተመዝግቧል።

ፋሽስት ጣሊያኖች በከፋፍለህ ግዛ መመሪያቸው ኢትዩጵያን በስድሰት የጎሣ ክልል ሸንሽነው ሌሎች ጎሣዎችን በፀረ-ዐማራና ኦርቶዶክስ ክርስታና የጥላቻ ቀስቅሰ አነሳስተዋል።

የጣሊያን ሶላቶዎች በምሥራቅ አፍሪቃ የቄሳር ግዛታቸው በክብር፣ በመብት፣ በጥቅም፣ በማኅበራዊ አገልግሎት የአርትራ ሃማሴንና የሱማሊያ ተወላጅ ባንዳ አስካሪዎችንና እስላሞችን የመጀመሪያ ምርጭያ ሲያደርጉ ያማራ ተወላጆችን ያገሉ እንደነበረ ዶክተር ላፒሶ ጌ. ድሌቦ ያደረጉት ጥናት ያረጋግጣል። ፋሽስቶች የኢትዩጵያን ሕዝብ የአንድነት መንፈስና የአርበኝነት ተጋድሎውን ለመግታት ከንቱ ሙከራ አድርገው መክሰራቸውን አልቤርቶ ሳባቺ የተባለው ጣሊያን በከፊል ገልጾታል። ያዲስ አበባ ጨፍጭያፊ ግራዚያኔ ከዱቼ ሙሶሎን በተላለፈለት ቴሌግራም ዐማሮችን በያለበት ሕፃን ሽማግሌ ሳይቀሩ ፍጅዋቸው፣ መሣሪያቸውን ማስፈታትና ፈጽሞ መደምሰስ፤ ወደፊት ከነሱ በኩል መበቀል እንዳይደርስብን መረጋገጥ አለበት። ሌላው ሕዝብ ፍላጎትየለሽ ብዙኃን መሪውን ከአስወገደን በቀለላሉ ለኛ ሰጥ ለጥ ብሎ ይታዘዛል። ሁሉም ይህን ማወቅ አለበቸው የተሳሳተ ስሜት ርሁርህነት እና ሰብአዊነት ቦታ የላቸውም፣ ዓላማችን የሮማ ቄሳር ግዛት መመሥርትና ማቆም ብቻ ነው፣

<< Es ist in meinenm Namen immer enthschiedner gegen die Rebellen vorzugehen, um sie entwaffnen und deren kleine und grosse amharische Führer vollständig zu eliminieren, damit eine Gegenaktion von ihrer Seite in Zukunft unterbunden wird: Die übrige Bevölkerung ist eine apathische Masse, die nach Liquidierung der Führer leicht von uns unterzuordnen ist. Alle müssten sich desssen bewusst sein. Die zivilien Funktionäre und militarischen Führer sollten das falshe Gefühl der Barmherigkeit und des Humanismus ablegen.. >> (Andrezeij Bartniki Geschichte Äthiopiens, Berlin, 1978, PP. 537. 538)

# የተማሪው እንቅስቃሴ የፋሽስት ጣሊያኖች ቀጣይ ፕሮፓጋንዳ

በፋሽት ጣሊያን ወራሪዎችና ተባባሪ ባንዳዎች የተጀመረው የዐማራ ጥላቻ ቅስቀሳና ዘመቻ በኢትዮጵያ አርበኞች የተባበረ ክንድ ድባቅ ቢመታም እንኳ በጓሮ በር በዘመናዊ ትምህርት ሽፋን በአዲስ አበባ የቀ.ኃ.ሥ ዩኒቨርስቲ ኮሌጅ ተማሪዎች ማኅበር የውጭ ኃይሎች አስተሳሰብና ተፅዕኖ ማራገፊያ መድረክ ሆኖ የፋሽስት ጣሊያኖችን ፀረ-ዐማራ ጥላቻን በሶሻሊዝም ካባ ጀቡነው ነዝተዋል። የተማሪው እንቅስቃሴ ቀንደኛ መሪዎች ከነበሩት አንደኛው የጅብሃ ማለትም የኤርትራ አርነት ግንባር ምልምል ኩታራው ወሎዬ ዋለልኝ መኮንን የኢትዮጵያን አጤ መንግሥት በማንኛውም መንገድ ለማስወገድ፣ ሕዝቡን ልክ በፋሽስቶች የጎሣ ክልል ዕቅድ መሠረት ለመሸንሸን በአስተማሪ ተብዬዎቹ ፀረ-ኢትዮጵያ የሆኑት እነ ሪቻርድ ግሪንፊልድ፣ ጆን ማርካኪስ ወዘተረፈ የተካነው ቅጥረኛ በእንግሊዘኛ ቋንቋ አዘጋጅቶ ያቀረበውን ይመለከቷል፣

<<**...**There is of course the fake **Ethiopian Nationalism** advanced by the ruling class and unwilingly accepted and even propagated by innocent fellow travelers. What is this fake Nationalism? ....>>

ያማርኛው ምላሽ፤

በእርግጥ ያለው የማስመሰል ኢትዮጵያዊ ብሔረተኛነት በገዥው መደብ የሚራመደውና ያለፈቃደኛነት የተቀበሉትና በአገር ኅብኝዎችም ጭምር የሚነዛው ነው። ይህ የማስመሰል ብሔረተኛነት ምንድን ነው?...ኢትዮጵያዊ ለመሆን ዐማርኛ መናገር፣ ያማርኛ ሙዚቃ መስማት፣ ኦርቶዶክስ ክርስትናን መቀበል፣ ሸማ መልበስ፣ ስምን መቀየር ነው።

ይህ ፀረ-ኢትዮጵያ ቅስቀሳ በቀጥታ የፋሽስት ጣሊያኖችና ቀጥሎም በድላችን ዋዜማ ኢትዮጵያን ለመርዳት መጣን ያሉት የእንግሊዝ ኢምፔሪያሊስቶች ኢትዮጵያን ከፋፍለው በሞግዚትነት የምሥራቅ አፍሪቃ ቅኝግዛታቸው አካል ለማድረግ ያዘጋጁት ነው። እንግሊዞች ኢትዮጵያን በሞግዚትነት ለመያዝ ያሰቡት ዕቅድ ሲከሽፍባቸው በሰሜን ደጋውን የኤርትራ ክፍል ከትግሬ ጋራ አጣምረው "ትግራይ ትግሪኝ" ወይም "ታላቋን ትግራይ" በመፍጠር ራስ ሥዩም መንገሻን የኤርትራና ትግሬ ገዥ አድርጎ በመሾም እንዲሁም በስተምሥራቅ "ታላቋ ሱማሊያ" እንድትፈጠር በመመኘት ጥቂት ግለሰቦችን መልምለው በሱማሌ ወጣት ሊግ ስም አድራጅተውና አሰልጥነው የጠነሰሱት ፀረ-ኢትዮጵያ ሴራ ከፍተኛ የሕይወትና ንብረት ጉዳት ማስከተሉ መቼም አይረሳም።

ቅጥረኛ ግልገል ባንዳዎች "ኢትዮጵያዊነት የይስሙላ ነው" ቢሉን አያስገርምም። አርበኝነትና ባንዳነት እሳትና ጭድ በመሆናቸው። በአጠቃላይ በማርክሳዊና ሌኒናዊነት ቱሪ ማንትሪ ጨንበል አጥልቀው የመላው ኢትዮጵያውያን ሕዝብ አኩሪ የአድዋ ድልም የይስሙላ ታሪክ ነው፣ ያምስቱ ዓመት ፀረ-ፋሽስት የኢትዮጵያ አርበኞች ተጋድሎትና ድልም የውሸት መሆኑ ነው! መቼም በቅጥረኛ ግራ ተብዬ ባንዳዎች አመለካከት የኢትዮጵያ ሕዝብ ለነፃነቱ ጎሣና ሃይምኖት ሳይለይ እጅ ለእጅ ተያይዞ በፀረ-ቅኝ ግዛት ተስፋፊዎችና በፀረ-ፋሽስት ተጋድሎ የከፈለው ክቡር መስዋእትነት የለም።

ለመሆኑ ሸማ መልበስ፣ ያማርኛ ልዩ ልዩ መዚቃ መስማት፣ እንጀራ መብላት. በሬ ጠምዶ ማረስ፣ ያማርኛ ግእዝ ፊደል ቆጥሮ ማንበብ መጻፍ ወዘተረፈ ሁሉ <u>ኢትዮጵያዊ</u> የጋራ ባሕልና ታሪክ አይደሉም ከተባለ ስለምን ባንዶችና ተራማጆች እንጀራችን ይበላሉ? ስለምንስ በአበሻ ጌጣጌጥና ውብ ሸማችንን ይለብሱታል? በኛ አልባሳቶች እንደ ለምድ፣ ጎፈሩ፣ አንፋሮ፣ ካባ፣ ጥልፍ፣ ጥበብ ኩታ፣ ጃኖ፣ ነጠላ፣ ወረቀ ዘቦ፣ ቀሚስ፣ ጦሊት፤ ራስ ማሰሪያ፣ ዐልቦ፣ ዐይነ ርግብ ወዘተረፈ እያጌጡ ዐማራውንን ማብጠልጠል ምን ይሉታል? ኩሉም በላይ አስገራሚው ጉድ፤

<<ኢትዮጵያ የሚባል **የጋራ አገር፣ ኢትዮጵያዊ የጋራ ባሕል፣ ታሪክና ሃይማኖት** ወዘተረፈ የለም። በተጨባጭ ያሉት የኦሮሞ ብሔር፣ የትግሬ ብሔር፣ የጉራጌ ብሔር፣ የሰዳሞ ብሔር፣ የሱማሌ ብሔር ወዘተረፈ ናቸው>> እያለ ዋለልኝ መኮንን ከሶቬዬት ሕብረት ፍጹም አረመኔ አምባገነኖችና ሕዝብ ጨፍጭያፊዎቹ እነ ሌኒንና ጆሴፍ ስታሊን የሰማውን የብሔር/ብሔረሰብ ሐተታ ያለምንም ታሪካዊና ማኅበረሰባዊ ማገናዘብ የሰማውን አንደ በቀቀን የኢትዮጵያ ተማሪዎች ማኅበርን በመድረክነት ተጠቅሞ በማስተጋባት፤ "**ኢትዮጵያ የጎሳዎች እሥር ቤት ናት**" በማለት በተለይም ለኤርትራ ተገንጣይ ነፃ አውጭ ተብዬ ቅጥረኛ ቡድኖች ዋና ተባባሪና አቀንቃኝ፣ በኢትዮጵያ የጎሣ ፖለቲካን ከፋሽስት ጣሊያን መባረር መልስ ቀንደኛው አራማጅ ከግበረ አበሮቹ የጀብሃ አባላት ጋራ ተገቢ ዋጋውን አግኝቷል። የተማሪው እንቅስቃሴ በአውሮፓና ሰሜን አሜሪካ በቡድነኛነት አባዜ ጎራ ለይተው በጎሣ ፖለቲካው ሲነታረኩ፣ ርስ በርስ ለመጠፋፋት አመቺውን ጊዜና ስፍራ ሲጠባበቁ ድንገት ሳያስቡት የኢትዮጵያ ሕዝብ አብዮት በየካቲት ወር 1966 ዓም. ፈነዳ። ግራ ኃይል ተብዬዎች በፍጥነት ገስግሰው አዲስ አበባ ገብተው አብዮቱን በኮሚኒስታዊ ሥርዓት መምራት ያለብንና መንገሥ ያለብንም እኛ ነን እንጂ ወታደራዊ ደርግ አይደለም ብለው ተፋጠጡ። ተፋጠጡ።

በዚህም ምክንያት ርስ በርስ ተጨራረሱ።
እራሳቸውን ሥር-ነቀል ለውጥ አራማጅ ተብዬዎች የሚያነበንቡት "ብሕር/ብሔረሰብ" የሚባልና "የጎሣዎች የራስን እድል በራስ መወሰን እስከ መገኘጠል" የተሰኛው የምሥራቅ አውሮፓ እስታሊናዊ የተውሶ መፈክር በኢትዩጵያ ምድር ፈጽሞ የማይሠራ፣ ዐማራውን ወገን ለይቶ በጠላትነት መፈረጃው "ጨቋኝ ብሔር፣ ትምክህተኛ፣ ቅኝ ገዥ፣ ገዥ መደብ፣ ነፍጠኛ ወዘተረፈ" በማለት የተነዛው ፕሮፓጋንዳ ጥንታዊቷን የጥቁር ሕዝብ አገር በባንቱስታን አፓርታይድ የጎሣ ክልል ማለትም የጎሣ እሥር ቤር ሸንሽነው ለማመሳቀል፣ ሕዝቡ ኢትዩጵያዊ ማንነቱን ዘንግቶ በጎሠኝነት ርስ በርስ ተገጭቶ እንዲተላለቅ፣ በመጨረሻም ጥቂት የጎሣ ሊሂቃን በአቋራጭ ከሥልጣን ኮርቻ ላይ ወጥተው በቅጥረኛ ወኪልነት ለመኖር የሚጠቀሙበት ስልት ነው።

# ብሔርና ጎሣ

በኢትዩጵያ ውስጥ ብሔር/ብሔረሰብ፣ ጎሣና ዘር የመሳሰሉት ቃላት ትልቅ ማወናበጃ ከሆኑ ቆይተዋል። እንደሚታወቀው ብሔር የግእዝ ቃል ትርጉሙ ቦታ፤ ሰፈር፣ ስፍራ፣ በአገር ውስጥ ያለ አውራጃ፣ ግዛት፣ በወሰን በድንበር የተለይ ነው። አገር ሲባል ደግሞ ሕዝብና መንግሥታዊ ድርጅት ያለው ልዕላዊ የግዛት ወሰኑ የታወቀ በቋንቋ፣ በሥርዓተ መንግሥት፤ በሕግ ሥርዓቱ የተለየ ማኅበረሰብን ያጠቃልላል። መንግሥት ጥንትም ሆነ ዛሬ በዘር፣ በሃይማኖትና በጎሣ መሥፈርቶች አይገለጽም። በኢትዩጵያ የአጤ መንግሥት ከጥንት ግብፅ የፈርዖን ሥርዓተ መንግሥት ምሥረታ በፊት ጀምሮ የነበረና ባላባታዊ ሥርዓተ ማኅበር እስከ 1967 ዓም ድረስ መኖሩ ሃቅ ነው። ሆኖም ግን የኢትዩጵያ የባላባት ሥርዓት ከአውሮፓው ፊውዳላዊ ሥርዓተ ማኅበር ጋራ ሲወዳደር ፈጽሞ የተለየ ነው። ኢትዩጵያ በዓለም ላይ በአገርነት ከሚታወቁት አንጋፋ አገሮች አንዷ ሆና ስትሰፋና ስትጠብ መኖሯ ይታወቃል።
በአውሮፓ ከመካከኛው ዘመን ፊውዳላዊ የአገዛዝ ሥርዓት ከተዳከመ በኋላ ልዩ ልዩ አገሮች ተመስርተዋል። ለምሳሌ፣ የፈረንሳይ፣ የእንግሊዝ፣ የስፔን፣ የፖርቱጋል፣ የጀርመን፣ የሩሲያ፣ የቱርክ ወዘተረፈ ይገኙበታል።
ከፈረንሳይ አብዩት ወዲህ በአውሮፓ አህጉር ብሔራዊ መንግሥት (Nation State) በተለይም በ20ኛ ክፍለ ዘመን የመጀመሪያ አጋማሽ ከ፩ኛው የዓለም ጦርነት በኋል ብዙ አገሮች ተቋቋመዋል።
በኮምኒስቶች ርዕዩት ብሔር የሚኖረው ታሪካዊ ማኅበረሰብነት ያላቸው ሰዎች በአንድ የጋራ ግዛት፣ የጋራ ምጣኔ ሃብት ትስስር፣ የጋራ ሥነ ጽሑፋዊ ቋንቋ እንዲሁም አጠቃላይ ባሕርይና ባሕላዊ መለያ ሲፈጥሩ ነው።
በማርክሳውያን ትንታኔ ያባላባት ሥርዓተ ማኅበር ወድቆ ካፒታሊዝም ሲተካና የሕብረተሰብ በመደብ የመከፋፈል ግንኙነት ላይ የተመሠረተ ማዕከላዊነት ብሔርን እንድሚያጠናክረው ገልጸዋል። ብሔርን ከዘርና ከነገድ ጋራ አሳስተውና ዘላቂነት የሚኖረው የተወሳሰብ የሥጋ ዝምድና የነገድ እድገት ግኝት ዘላለማዊና ተፈጥሯዊ ከታሪክ በላይ የሆነ ክስተት አስመስለው የሚቀዣብሩት ወገኖች ተነቅፈዋል።
በዓለም ላይ አንድ ወጥ የሆነ (Homogeneous) ብሔር /አገር/ የለም። የሁሉም አገሮች የእድገት መነሻ ምንጭያቸው የልዩ ልዩ ነገዶች ውህደት ነው። አያሌ አገሮች (ብሔሮች) አሜሪካን ጨምሮ የተመሠረቱት ከተለያዩ ነገዶች ብቻም ሳይሆን ከተለያዩ ዘሮችም ጭምር ነው። በዘር አንድ ዐይነት መሆን የአንድ ብሔር ወይም አገር መገለጭያ አይሆንም። ነገዳዊ መለያ እንደ ቋንቋ፣ ባሕልና ልማድ እነዚህ ሁሉ በሥነ ሕይወታዊ (Biological) የተወሰኑ ሳይሆኑ የማኅበረሳባዊ መስተጋብር ውጤቶች ናቸው። ደንባራ ግራ ኃይል ተብዬ ጎሠኞች ያውሮፓን የብሔር ትርጉምና ታሪካዊ ሂደት ሳያውቁ በኢትዩጵያ ውስጥ በፍጹም ለሌለ ነገር መጠቀሚያ አድርገውታል።
በኢትዩጵያ የዐማራ ብሔር? የኦሮሞ ብሔር፣ የጉራጌ ብሔር፣ የሲዳማ ብሔር፣ የሱማሌ ብሔር፣ የትግሬ ብሔር ወዘተረፈ የሚባሉ አገሮችነ መንግሥታት አልነበሩም፣ የሉም?

የሌለውን ነገር እንዲኖር ታስቦ ነው የጎሣ ክልል ማለትም የጎሣ እስር ቤት በውጭ ጠላቶቻችን ድጋፍና ትብብር አገር በቀል ቅጥረኞቻቸውን እነወያኔ ትግሬ፣ ሻቢያና ኦነግን ከወታደራዊ ደርግ ውድቀት ግንቦት ወር 1983 ዓ.ም በኋላ ዐማርኛ ተናጋሪውን ብቻ አግልለው፣ በሰኔ ወር በተደረገው ጉባዔ ላይ ኤርትራ እንድትገነጠል፣ በቀሪው አገር የባንቱስታን አፓርታይድ የጎሣ ፖለቲካ እንዲነግሥና መገነጣጠል እንዲያመች ተስማምተው የሽግግር መንግሥት ተመሥርቷል።

የጎሣ ክልል ካርታ የተዘጋጀው በነሐሴ ወር 1983 ዓ.ም 10 አባላት ባሉት ስብስብ ሲሆን ሦስት ከወያኔ-ኢሕአዴግ፣ ሁለት ከኦነግ፣ አንድ ከጉራጌ፣ አንድ ከሃድያ፣ አንድ ከሐረሬ፣ አንድ ከሱማሌና አንድ ከአፋር ነበሩ። ሁሉም በቅርጭያው ላይ ከፍተኛ ድርሻውን ለማግኘት ሲፋለሙ እንደነበር ሳራ ቫውጋን (Sarah Vaughan : Ethnicity and Power in Ethiopia, The university of Edinburgh (2003) pp.33-34 (https://www.era..lib.ed.ac.uk/bitstream/id/1299/Vaughanphd.pdf ) ያደረገችው ጥናት ያረጋግጣል።

የኦነግ ተወካይ የነበሩት የወሎን ክፍለ ሀገር በጠቅላላው ታሪካዊ ግዛታችን ነው በማለት ወደ "ኦሮሚያ" እንዲከለል ሲጠይቁ የሃድያው ተወካይ እንዲህ ከሆነማ ባሌና አሩሲ የሃድያ ሲዳማ ክልል መሆን አለባቸው በማለት የኦነግን ጥያቄ ስለተቃወሙት እድሜ ለሃድያ ኢትዮጵያውያን ወለዬዎች በግዳጃ ወረሞ ከመሆንና በቁቢ ፊደል ጥቁር ፈረንጅ ከመሆን ለጊዜው ተርፈዋል። ነገር ግን የየረር ናዝሬት፣ ያሩሱ፣ የባሌ፣ የሐረርጌ፣ የሸዋ ሰሌሌ፣ የተጉለት ወግዳ፣ የመራቤቴ ደራ ወዘተረፈ ዐማሮች ዕጣ ፋንታቸው በወያኔ-ሻዕቢያ ትግሬ ትዕዛዝና በተለጣፊዎች አስገዳጅነት ወረሞ መሆን ብቻ ሆኗል። የኢትዮጵያ ምድር በጎሣ መለያ ተሸንሽና የታሪካዊ ጠላቶቻችን መፈንጭያ ስለሆነች ለም መሬቷ ለቅርምት፣ ሕዝቧ ለስደትና ለአረብ ባርነት ተዳርጓል። በእንቅርት ላይ ዶሮ ድግፍ እንዲሉ በመላው አገር በወያኔ ትግሬ አዝማችነትና በተለጣፊ ታጣቂዎች በያለበት የጎሣ ማጽዳትና የዘር ማጥፋት ዘመቻው ተስፋፍቶ ይገኛል።

## ጎሠኝነት

በኢትዮጵያ ጎሠኝነት የተጠነሰሰው በአውሮፓ ቅኝ ገዥ ተስፋፊዎች ሲሆን የተዘራውና በምቹ ማሳ ላይ የበቀለውና የለመለመው በቀኃሥ ዩኒቨርስቲ የተማሪዎች ማኅበርና እንዲሁም በውጭ ሃገራት ማለትም በአውሮፓና ሰሜን አሜሪካ ለከፍተኛ ትምህርት በተላኩት ተማሪዎች ዘንድ ነበር። ዘርና ጎሣ አንድ አይደሉም። ጎሣ ቋንቋን እንጅ ዘርን አያመለክትም። ጎሠኝነት እራስ ወዳድነት፣ ስግብግብነት፣ ይሉኝታቢስነት የኔ ቋንቋ ተናጋሪ ወገን ከሌላው ሰው ይበልጥብኛል ብሎ መጥቀም፣ መጠቃቀም፣ ማዳላት ነው። በአንድ የተለያዩ ነገዶችና ማኅብረሰቦች አብረው በጋራ በሚኖሩበት አገር ውስጥ ጎሠኝነት ሁሉን ለኔ ጎሣ አባላት ብቻ በሚል ጭፍን ሐገ ወጥ ድርጊት ማድረግ ነው። ለምሳሌ በአጤ ኃይለ ሥላሴ ዘመን የልማትና የእድገት አውታሮች ትኩረት የተሰጠው ለኤርትራ ነበር። ለዚህም ዋናው ምክንያት የኤርትራ ተወላጆች ማንም ሳያስገድዳቸው ለነፃነታቸውና ለኢትዮጵያዊነታቸው የእንግሊዝን ቅኝ ግዥዎች ታግለው ከሌሎቹ ወንድሞቻቸው ጋራ የተቀላቀሉ ስለሆነ ነው። ነገር ግን የኤርትራ ተወላጅ ከፍተኛ የመንግሥት ባለሥልጣናት በጎሠኝነት ተለክፈው ባሉበት መሥሪያ ቤት ሁሉ በብዛት የሚቀጥሩት የጎሣቸውን አባል ብቻ ሲሆን የጣሊያን ቂጣ ጋጋሪና ተላላኪ አውቆ ፈረጅ በመሆናቸው ሌላውን ኢትዮጵያዊ በንቀት የሚመለከቱት የነበሩትና ያሉት። ይህም የፈጠራ ወሬ ሳይሆን ዓለም ያወቀው ፀሐይ የሞቀው ነበር።

<< Those Eritreans who serve the government have often been accused of lording it over other Ethiopians: more exposed to European influences, some Eritreans have tended to look down upon other Ethiopians newly introduced to the Europeanizing aspects of modern Ethiopia**.** A common complaint in Ethiopian government circles is that Eritreans are to clannish and that to place one Erirrean in charge of an office ist to introduce the proverbial camel" nose into the tent and end end up with an office full of Eritreans.>>

(Ropert L Hess: Ethiopia the morernization of Autocracy, Cornell University press, (1976), p.191)

በጎሠኝነት የተለከፉት ግራ ኃይል ተብዬዎች፣ የጦር ኃይል አባላትና የተለያዩ የሕብረሰብ ክፍሎችም ነበሩ። የደርግ ወታደራዊ መንግሥት አባላት በአብዛኛው ወረሞች ሲሆኑ በሲቪል ግራ ተብዬ የጎሣቸው አባላት እየተዘወሩና እየታገዙ በጎቡዕ ለኦሮሞ ብሔረተኛነት በአብዮት ሽፋን አረምደዋል።

በኢትዮጵያና በዓለም ላይ በታሪክ ሰነድ ጋላ በመባል የሚታወቀውንና የሱማሌ ጎሣ ያወጣላቸውን የጎሣቸውን መጠሪያ ስም በደርግ አዋጅ ኦሮሞ ተብለው እንዲጠሩ፤ አሩሲ መባል ቅርቶ አርሲ ወዘተረፈ እያሉ አሳውጀዋል። እንዲሁም ከጋላ ወረራ በፊት ለምሳሌ በጥንታዊው ባሌ ክፍለ ሀገር የሚገኘውን የፉሲል ተራራ ባቱ በሚል ስም አስለውጠውታል። በፋሽስት ጣሊያኖች የተነደፈው የፀረ ዐማራ ብሔረተኝነት ጅኒ በተማሪዎች እንቅስቃሴና በደርግ አምባገነን አማካይነት ተከቶበት ከነበረው ሙዳይ ውስጥ ክዳኑ ተከፍቶለት በዝግታ ሲራመድ ቆይቶ ደርግ ሲገረሰስ ከቀድሞው በተለየና በተጠናከር ሁኔታ ለማጥቃት ተናኝቷል።
ፀረ ኢትዮጵያ ተገንጣይ ቡድኖች እነ ወያኔ፣ ሻዕቢያ፣ ኦነግ፤ ወዘተረፈ በኢትዮጵያ የተደረገውን ማኅበራዊ ቀውስ ለጠባባ ጎሠኝነት ዓላማቸው ማሳኪያ ስልትና ዘዴ አድርገውታል። ለጠቅላላው ለኢትዮጵያ ሕዝብ እድገትና ልማት፣ ለዲሞክራሲያዊ ሥርዓተ መንግሥት ምሥረታ ሳይሆን ለግል አምባገነናዊ ሥልጣን ማስፈኛና ማስፈኛና በቅጥረኝነት ለባሕር ማዶ ወዶ አሽከርነት ነበር።
ለምሳሌ አደሬው የጦር መኮንን አብዱላሂ ዑመር ተጨቆንኩ የሚለውና በአገራችን ውስጥ ጭቆና አልነበረም አልልም እያለ ያላዘነው ዋናው ምክንያት ከሸዋ ይፋት ማዕከል ወደ ሐረር በ15ኛው ክፍለ ዘመን የተዛወሩት ወላስማዎች በግራኝ አሕመድ አልጋዚ መሪነት፤ በአረብና ኦቶማን ቱርክ ርዳታ የኢትዮጵያን አጤ መንግሥት አሶግደው ለማስለም ያደረጉት ያ15 ዓመታት ወረራና የባሕል ውድመት ዘመቻቸው ሲከሽፍባቸውና በተከተለውም የጋላ ዘላን ሉባ ወራሪ ሐረር ከተማ ስትከበብ መከላከያ ጀጎል ገንብተው የሚኖሩት ለክርስቲያን ኢትዮጵያውያን ያላቸው የጥላቻ ስሜት ሰር የሰደደ ሆኖ ያደሬ፣ የሱማሌና በግብፅና ቱርክ አስገዳጅነት የሰለሙት ቆቱዎች የሱኔ እስላሞች ዘወትር ወደ ግብፅ ካይሮና አረቢያ ሠርፀ ምድር እያንጋጠጡ ጥቁር አፍሪቃዊ አበሻ መሆናቸውን ክደው አረብ ነን እያሉ ይቃዣሉ። ግመል ነጅው ጀማላ አረብ ደግሞ "አበሽ ባሪያ" ይላቸዋል እንጁ ከሰውም እንኳ አይቆጥራቸውም። አብዱላሂና ብጤዎቹ ለምን ሐረርጌ ከግብጽና ቱርክ ለቆ መውጣት በኋላ በሸዋ የምኒልክ ጦር ተያዘችና መልሳ የኢትይጵያ አካል ሆነች በማለት ነው። ሐረር ከተማ ያለምንም ደም መፋሰስ በሸዋ ጦር ተይዛ ከፍተኛ እድገት አድርጋለች። ፋሽስት ጣሊያኖች ሐረር ከተማ ሲገቡ ለሦስት ሣምንታት ያህል ዐማራውን ሕዝብ ለይተው ፈጅተውታል። የፋሽስቶች የአምስት ዓመቱ ወረራ በአርበኞች ወደርየለሽ ተጋድሎ ድብቅ ተመቶ ሲያከትም ሐረር የገቡት የእንግሊዝ ጦር ባለሥልጣኖች የአደሪ ተጠሪዎችን ሰብስበው ከኢትዮጵያ ተገንጥላችሁ በእንግሊዝ ሞግዚትነት የራሳችሁን ነፃ መንግሥት አቋቁሙ ተብለው እንደ ነበር አይዘነጋም። ከዚህም ሌላ የእንግሊዝ የውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር ኤርንስ ቢቭን ለሀገሩ ፓርላማ ባደረገው ንግግር የኢትዮጵያን ኡጋዴን አውራጅ ጨምሮ በአፍሪቃ ቀንድ የሚገኙት ዘላን ሱማሌዎችን በሙሉ በእንግሊዝ አስተባባሪነት በአንድነት ተደራጅተው "ታላቋ ሱማሊያ" መፈጠር አለባት። ለዚህም ተግባራዊነት የሰማሌ ወጣት ሊግን ሃርጌሳ ውስጥ እንዲደራጅ አደርገዋል።

# የደርግ ጭፍጨፋና የአማን አንዶም ዕረፍት

ፋሽስት ጣሊያን ድባቅ ተመታ ከተባረረች በኋላ የአጤ ኃይለ ሥላሴ መንግሥት ከባዶ ተነስቶ ኢትዮጵያን ወደ ሃያኛው ክፍለ ዘመን ለመግባት ያሽቻላት አዲሱ የተማረው ኃይል በትምህርቱ፣ በልምዱ፣ በውጭ ፀረ-ኢትዮጵያ ኃይሎች ተጽዕኖ ሰር ሆኖ ያገሩን ታሪክና መኅበረሰብ በንቀትና ጥላቻ. በባዕድ እምነትና የማስመሰል ሥልጡንነት የተደናበሩት የአጤውን ባሕላዊ መንግሥት የፍትሕ ጉድለትና የአስተዳደር በደልና ድክመት ለማረምና ለማቃናት ሳይሆን መንግሥቱን ከሥር መሠረቱ ለማጥፋት ሲያደክሩ በተፈጠረው ውጭያዊና የአገር ውስጥ ሁኔታዎች የየካቲት ወር 1966 ዓ.ም ተከሰተ። ያጤው መንግሥት ያለምንም የተቃውሞ ርምጃ ተንኮታኩቶ ደርግ መስከረም 2 ቀን 1967 ዓ.ም አጤ ኃይለ ሥላሴን ከሥልጣናቸው አውርዶ ራሱን ጊዜያዊ ወታደራዊ መንግሥት ነኝ ብሎ አወጀ። የደርግ አባል ያልነበሩትን ጀግናውን ጀነራል አማን አንዶምን የደርጉ ሊቀ መንበርና ርዕሰ ብሔር አድርጎ ሾሟቸው ነበር።
<<ያለምንም ደም ኢትዮጵያ ትቅደም>> በሚል መፈክር ሲያነበንብ የቆየው ደርግ በመንግሥቱ ኃይለ ማርያም ቀንደኛ መሪነት ሕዳር 12/13 ቀን 1967 ዓ.ም 59 ሰዎችን እንበለ ፍትሕ ጨፍጭፎ በጅምላ መቃብር ቀበራቸው። በዚሁ ዕለት ነው ርዕሰ ብሔር ሆነው የተሾሙት ጀነራል አማን አንዶም ቤታቸው ተከቦ ተታኩሰው ሲሞቱ ሌሎች ሁለት የደርግ አባላትም በግፍ ከተገደሉት ውስጥ ይገኙበታል። ለሀገር ደህንነት አስበው በሰላም እጃቸውን ሰጥተው በእስር ላይ ከነበሩት ያጤው መንግሥት ከፍተኛ ባለሥልጣናት 17 ጀነራሎች፣ ሁለት ጠቅላይ ሚኒስትሮች ከእሥር ቤት ተወስደው ያለፍርድ በጨለማ ኃይሎች ተረሸነዋል።

እርግጥ ነው ጀነራሉ ከብዙ አገር ወዳዶች በተለይም ከመረጃ ባለሙያው ብ/ጀነራል የመልኬ ጌታነህ የተነገራቸውን ምክርና ትብብር ባለመስማት በአንጻሩ በመሰሪውና ከሃዲው በረከተ አበ ሃብተ ሥላሴ ውትወታ ተሳስተው የሕይወት ዋጋ ከፍለዋል።
እዚህ ላይ መታወቅ ያለበት ዐቢይ ጉዳይ አለ። ለዚህ ፍጹም አረመኔያዊ ጭፍጨፋ ተጠያቂ ደርግ ብቻ ሳይሆን ሲቪል ግራ ኃይል ሥር ነቀል ለውጥ ፈላጊ ተብዬዎችም ተሳታፊዎች ነበሩ። በታሠሩት በዝባዥ፣ አድኃሪያን ላይ በአስቸኳይ እርምጃ ይወሰድ፤ ኃይለ ሥላሴ ይሰቀል፣ እንዳልካቸው ይሰቀል፣ ወዘተረፈ እየተባለ ልዩ ልዩ የሕቡዕ ቡድኖች በራሪ ወረቀቶችን በትነዋል። ለምሳሌ እንደ ቀይ ባንዲራ፣ አብዮት፣ ዲሞክራሲያ፣ ሰፊው ሕዝብ ወዘተረፈ ያሉት ሰፊ ቅስቀሳ ማድረጋቸው ከቶ አይዘነጋም። አብዮት የራት ግብዣ አይደለም፤ ያለደም አብዮት የለም... እያሉ ለአራጆች ቢለዋ አቀራቢዎች ነበሩ። በፈረንሳይ፣ በሩሲያ፣ በቻይና ወዘተረፈ የተደረገውን ጭፍጨፋ በኢትዮጵያ ሕዝብ ላይ ለመድገም ሁኔታውን አመቻችተዋል።
ለደርግ አረመኔያዊ ርምጃና ለኮምኒዚም ሶሻሊዝም ርዕዮተ ዓለም አቀንቃኝነት ያዘጋጁት ሲቪል ማርክሳውያንና ሌኒናውያን ተብዬ አወናባጆች እነዚህም በአብዛኛው ለትምህርት በተላኩበት የምዕራብ አውሮፓና ሰሜን አሜሪካ ምሽጋቸው ከቅድመ አብዮት በፊት ቡቡድነኛነት ጎራ ለይተው የተለየ ሃሳብና አመለካከት ያለውን ወገንና ግለሰብ ሁሉ እንደ ዋና ጠላትና ከሃዲ ቆጥሮ ማብጠልጠልና ለፍልሚያ ግድያ መፈላለግ ዋና ተግባራቸው ሆኖ ላይ ታች ሲቃዡ ድንገት አብዮቱ በጭራሽ በአሳሰቡትና ባልጠበቁት ወቅት ስለፈነዳ የተፈጠረውን መልካም አጋጣሚ ለመጠቀም አዲስ አበባ ሮጠው ገብተዋል።
ጊዜያዊ ወታደራዊ መንግሥት ሥልጣን ለሕዝብ አስረክቤ ወደ ጦር ሰፈሬ እመለሳለሁ እያለ ሲዋልል የርዕዮተ ዓለም ባለሙያ ስለአልነበረ የኢትዮጵያ ሕብረተሰባዊነት (Ethiopian Socialism) ብሎ ባለ 10 ነጥብ መርሃ ግብር ታሕሣሥ 10 ቀን 1967 ዓ.ም አወጀ። እፍኝ የማይሞሉት የአገር ውስጥና ከውጭ የተመለሱት የሥር-ነቀል ለውጥ አቀንቃኝ ግራ ኃይል ተብዬዎቹ ግን ከሳይንሳዊ ሶሻሊዝም በስተቀር ሌላ መንገድ የለም ብለው አወገዙት። የኢትዮጵያ አንድነት፣ ልዑላዊነት፣ ፍጹምነት ብሎ ነገር የለም። ይህማ ፍጹም ፋሽስታዊነት ብለው በማውግዝ አሁኑኑ እኛ ሥልጣኑን ወሰደን ኮሚኒስታዊ ሥርዓት እንገነባለን ብለው አመጽ ቀሰቅሰው አገር ትውልድ አወደሙ።

# ምን ማድረግ ይበጃል?

ዐማራው በፀረ-ኢትዮጵያ ኃይሎች፣ በጎሣ ፖለቲካ፣ በገንጣይ አስገንጣይ ቅጥረኛ ቡድኖች ተቀነባብሮ የሚደረስበትን ጥቃትና ሰቆቃ ለመቋቋም፣ የወል ደህንነቱን፣ ሰብአዊ መብቱንና ማኅበራዊ ጥቅሙን በማንኛው ጊዜና ስፍራ ለማስከብር አቅምና ችሎታ ያለው ስለሆነ ኩሁሉ በተቃዳሚ ደመላሽ ያማራ መከላከያ ኃይል በኅቡዕ ተደራጅቶ ጠላቶችን ለይቶ የሚደመስስ፣ በኢትዮጵያዊነታቸው ፀንተው ለቆሙት፣ ለነፃነታችን በጋራ መስዋዕትነት ለከፈሉት፣ ከዐማራ ወገናቸው ጋራ ተጋብተው፣ ተዋልደው ተዛምደው፣ ተስማምተውና ተከባብረው ለሚኖሩት ሁሉ ጋሻ መከታ የሚሆን ፈጥኖ ደራሻ ታጠቂ ኃይል ማደራጀት ነው። ኀሠኞች ታጥቀውና ተደራጅተው በወያኔ ትግሬ አዝማችነት በዐማራው ሕዝብ ላይ በያለበት በተነሱበት ጊዜ መሐል ሰፋሪዎችና ሆድ አደሮች ዐማራው ሕዝብ እንዳይደራጅ፣ ራሱን በአካልም ሆነ በሥነ ልቡና አዘጋጅቶ ከጠላቶቹ ለሚሰነዛሩበት ጥቃት አጸፋውን ለመስጠት ዝግጁ እንዳይሆን ያልፈነቀሉት ድንጋይ የለም። ፀረ-ዐማሮች ዘመቻቸውን የሚያቆሙት ዘወትር አቤቱታ በማቅረብ፣ የታሪክና ባሕል አንድነትና አብሮ መኖርን በመስበክ ሳይሆን ተገቢውን አጸፋ በመስጠትና በቆራጥነት ጠላትን ለይቶ በመምታት ነው። ዐማራው እራሱን በራሱ ካልረደና ራሱን ለመጠበቅ ከአልተደራጀና ከአልተዘጋጀ በስተቀር የሚደርስለት ሌላ ማንም የለም። ባለቤት ካልጮኸ ጎረቤት አይረደም እንዲሉ።
ኢትዮጵያ ተገንዛ በመቃብር አፋፍ ላይ ስትገኝ አገር ወዳዱ ግን ሁኔታውን ተረደቶ ርምጃ ሲወስድ አይታይም። አብዛኛው ሕዝቡ በወያኔ ትግሬ ቅጥረኛ ቆሽቱ በግኗል፤ ግራ ከመጋባቱም ሌላ ተስፋ ቆርጧል። ቆራጥ ታጋዮች ብቅ እያሉ በከፍተኛ ጉጉትና ተስፋ ሲታገሉ ውለው ሳያድሩ የወያኔ ትግሬና ቅልብ ተለጠፊዎቹ ሰለባ ሆነው ያታሰራሉ፣ ይገደላሉ፣ ይሰደዳሉ።
ተቃዋሚ ድርጅቶች እንኳን በገጠር ይቅርና በአዲስ አበባ ከተማ በሚፈለገው መንገድ መንቀሳቀስ እንዳይችሉ ሰለተደረገ ለትግሉ ወሳኝ አስተዋፅኦ አላደረጉም። የመኖራቸው ጠቀሜታ ለሕዝቡ አለኝታ ሳይሆን ለወያኔ ትግሬ ኀሠኛ የፈሪ በትር ማረፊያና የመደብለ ፓርቲ ማስመሰያ አጃቢነት ነው። ተቃዋሚ ድርጅቶች የተባሉት እግር ከወርች ተሰንገው ስለተዛዙ ሕዝብን ለመቀስቀስ ሰላማዊ ሰልፍ ለማድረግ እንኳ አይችሉም። ታዲያ! ምን ዓይነት ሰላማዊ ትግል? በመሆኑም ያለው ትክክለኛ አማራጭ ቢሮአቸውን ዘግተው <u>በሕቡዕ</u> መንቀሳቀስና ሕዝቡን በመላው ኢትዮጵያ በመቀስቀስ ወያኔ ትግሬን ማስወገደን ነው።
ሞት ለወያኔ ትግሬ!!
ድል ለኢትዮጵያ ሕዝብ!!

ተፈሪደኝ ኃይሌ (አባ መንጥር) ዘብሔረ ይፋት